# መመሪያ

## የMONTGOMERY COUNTY የትምህርት ቦርድ

የተዛመዱ ርእሶች፡- ACA፣ IGT-RA፣ JFA-RA፣ JHF-RA፤
ሃላፊ ፅ/ቤት፡- የተማሪና የቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ

# ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት

## A. ኣላማ

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ (Board) ት/ቤቶች ለመማር ሰላማዊ ቦታ እንዲሆኑ ከማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ከማስፈራራት ነፃ ለሆነ ኣካባቢ ግዴታ ገብቷል። ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ትምህርትን ረብሾ በኣከዴሚ ግኝት፣ ስሜታዊ ጤንነት፣ እና በት/ቤት ኣየር ኣሉታዊ ተፅኖ ሊያደርስባቸው ይችላል።

ቦርዱ በት/ቤት ንብረት፣ በት/ቤት ኣውቶቡሶች፣ ወይም በት/ቤት-ስፖሰር በሆኑ ትግባሬዎች የማንኛውንም ግለሰብ የቃል፣ ኣካላዊ ወይም የፅሁፍ (ኤሌክትሮኒክስን ጨምሮ) ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ለመከልከል ግዴታ ገብቷል።

ቦርዱ በተጨማሪ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ በሚያቀርቡ ግለሰቦች ወይም በሚሸማቀቁ፣ በሚመሰክሩ፣ በሚታዘቡ፣ ወይም ስለ ኣንድ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ተግባር ኣስተማማኝ መረጃ ባለቸው ላይ በቀል ወይም ግብረመልስ ለመከልከል ግዴታ ገብቷል።

## B. ጉዳዩ

የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት መከልከል እንዲሁም የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ በሚያቀርቡ ግብረመልስ መከላከል ከተማሪዎች፣ ኣስተዳደር፣ እና የት/ቤት ሰራተኛ የመከላከልና ጣልቃ መግባት ስልጠና የሚያካትት ስርኣት-ኣቀፍ ጥረት ይጠይቃል። የሚሸማቀቁ ተማሪዎች፣ እና ሌሎችን የሚያሸማቅቁ፣ የተለያዩ ትርጉም ያዘሉ የጤና፣ የደህንነት፣ እና የትምህርት ኣደጋ ተሞክሮዎች ሊደርሱባቸው ይችላል።

በዚህ የቦርድ መመርያ ኣጠቃቀም መሰረት፣ "ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት" ማለት በተማሪ/ዋ የትምህርት ጥቅሞች፣ እድሎች፣ ወይም ኣፈፃፀም፣ ወይም በተማሪው/ዋ ኣካላዊ ወይም ሳይኮሎጂካዊ ደህንነት ትርጉም ባለው ሁኔታ ጣልቃ በመግባት ኣሉታዊ ትምህርታዊ ኣካባቢ የሚፈጥር፣ የቃል፣ ኣካላዊ፣ ወይም ፅሁፍ ስነምግባር ወይም የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት ሆን ተብሎ የሚደረግ ስነምግባር ማለት ነው እናም፡-

1. በቦርድ መመርያ ACA፣ *ፀረኣድልዎ፣ ፍትህ፣ እና ባህላዊ ብቃት* እንደተገለፀው በገለሰቡ/ቧ ሃቀኛ/ተጨባጭ ወይም ይሆናል በተባለ የግል ባህሪይ በመነሳሳት፤ ወይም፣

2. ማስፈራራት ወይም እጅጉን የሚያሰጋ/ከባድ ዛቻ፤ እና፣

3. በት/ቤት ንብረት፣ በት/ቤት እንቅስቃሴ ወይም ክውነት፣ ወይም በት/ቤት ኣውቶቡስ ላይ ቢካሄድ፤ ወይም፣

4. የት/ቤትን ስነርኣታዊ ግብረት በመሰረቱ/በዋናነት ይረብሻል።

"የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ" ማለት ቴለፎን፣ ሞባይል ቴሌፎን፣ ኮምፒውተር፣ ወይም ታብሌትን ጨምሮ፣ በኤሌክትሮኒክ መሳርያ አማካይነት የሚሰራጭ/የሚተላለፍ መገናኛ ማለት ነው። ሳይበርቡሊይንግ/Cyberbullying፣ የማሸማቀቅ፣ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት አንድ ፎርም ነው። “ሳይበርቡሊይንግ” ማለት በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች በመጠቀም የሚተላለፍ መልእክት ማለት ሲሆን የማህበራዊ ሚድያ ጣቢያዎችንም ያካትታል። ሳይበርቡሊይንግ "የኤሌክትሮኒክ መገናኛዎች" ስር የሚውሉ ማናቸውንም የወደፊት መተግበርያዎችን ይጨምራል።

በዚህ መመርያ አጠቃቀም መሰረት ማሸማቀቅ በነዚህ ስይወሰን አካላዊ (መምታት፣ መግፋት፣ መገፍተር)፣ የቃል (ማብሸቅ፣ ማስፍራት፤ መገደድ፣ መቀለጃ መሆን፣ ስድቦች) ወይም ተዛማጅ (ጉምጉምታ፣ መተው ወይም መሰደድ/ማግለል)ን ሊያካትት ይችላል።

## C. አቋም

Montgomery County Public Schools (MCPS) ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራትን የመለየት ፕሮግራም ተግባራዊ ያደርጋል፤ ውጤታማ የሆኑ የመከላከያ ፕሮግራሞችን ይተገብራል ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ሲከሰቱ ጣልቃ ይገባል፤ የጣልቃገብነት ስልቶችን ይተገብራል፤ ካስፈለገም የውጭ መጣቀሻ/ማስተላለፍያም ያቀርባል። በት/ቤት ውስጥ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት፣ እና በማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ በሚያቀርቡ ግለሰቦች ላይ በቀል ወይም ግብረመልስ መከልከል፣ እንዲሁም ውጤቶችና ማስተካከያ ተግባሮች/መፍትሄዎች የስርኣት-አቀፍ መከላከያና ጣልቃገብነት ፕሮግራም አካል ሆነው መካተት ይኖርባቸዋል። የዚህ አይነቱ ፕሮግራም ክፍለ-አካሎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

1. መከላከል እና ጣልቃገብነት

    a) ኣመታዊ ሞያዊ እድገት ለአስተዳዳሪዎችና ለሰራተኛ ኣባሎች ስለ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ብዛት፣ መነሻዎች፣ እና ውጤቶች ንቃታቸውንና ግንዛቤያቸውን ለመጨመር፣ እና ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ለመከላከል በምርምር-የተመሰረቱ ስልቶች፣ ማረሚያ እርምጃዎች፣ እና ውጤቶች መጠቀምን ለመጨመር። ሞያዊ እድገት ለተማሸማቀቁ ተማሪዎች፣ ላሸማቀቁ ተማሪዎች፣ እና ለዳር ቆሞ ተመልካች ተማሪዎች እንዴት ምላሽ መሰጠት እንዳለበትም በተጨማሪ ማካተት ኣለበት።

    b) የእኩያ ድጋፍ፣ እርስበርስ መከባበር፣ ለህብረ-ብዙህነትና ለባህል ስሜታዊነት የሚያበረታቱ ፕሮግራሞችን የመሳሰሉ በማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት በመከላከል ጥረቶች የተማሪ ተሳትፎ።

    c) ስለ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ብዛት፣ መነሻዎች፣ እና ውጤቶች እና ልጆቻቸውን ስለ መደገፍ ስልቶች ለወላጆች/አሳዳጊዎች ለማሳወቅ ከቤተሰቦችና ከማህበረሰቡ ጋር መግባባት እና ግንኙነት ማድረግ።

    d) ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት የህዝብ ጤንነት ኣደጋ መሆኑን እና ለተሸማቀቁ ተማሪዎች፣ ላሸማቀቁ ተማሪዎች እና ለዳር ቆሞ ተመልካች ተማሪዎች የጤና መገልገያዎች እንዳሉ ለማሳወቅ ከማህበረሰብ ጤና እና የኣእምሮ ጤና መገልገያዎች ጋር ትብብሮሽ።

    e) የተሸማቀቁ ተማሪዎች ደህንነት እየተጠበቀ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራትን ለመከላከል የተለያዩ ጣልቃገብነቶች ዳብረዋል።

2. የሚያስከትሏቸው መዘዞችና የመፍትሄ እርምጃዎች

የሚያስከትሏቸው መዘዞችና የመፍትሄ እርምጃዎች ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራትን ለፈፀሙ ግለሰቦች፤ በበቀል ወይም በግብረመልስ ላይ ለሚገኙ ግለሰቦች፤ እና ስለ ማሸማቀቅ ሃሰተኛ ክስ የመሰረቱ ግለሰቦች በፀናና በፍተሃዊ መንገድ በMCPS ደንብ JFA-RA፣ *የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች መሰረት* መዳኘት አለባቸው።

3. የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ተግባሮች ዘገባ አቀራረብ ቅደም-ተከተሎች

ስርአቱ ለት/ቤቶች የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራትን ተግባሮች ዘገባ ለማቅረብ አመቺ፣ ደህና፣ ግላዊነታዊ፣ እና ለእድሜ-አግባብነት ያላቸው ቅደም-ተከተሎች ማቅረብ አለበት።

b) ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ እና ወላጆች ፣ በያንዳንዱ ት/ቤት ስለ ዝገባ ቅደም-ተከተሎች እና የMCPSን ፎርም 230-35 *ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም የማስፈራራት ዘገባ ፎርም* መኖርን ጨምሮ እንዲያውቁ ይደረጋል።

የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ኣድራጎቶች ዘገባ በMCPS መደፋፈርና መደገፍ ኣለበት። MCPS ዘገባ ማቅረብ/ማስታወቅ የሚሸማቀቁ ተማሪዎችን፣ የሚያሸማቅቁ ተማሪዎችን፣ እና ዳር ቁሞ ተመልካች ለሆኑ ተማሪዎች ለማገዝ እንደሚያመራ ግልፅ መልእክት ማስተላለፍ ኣለበት።

4. የፈጣን ምርመራ ትግባሬዎች ቅደም-ተከተሎች ለማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት

a) ርእሰመምህሩ/ሯ ወይም ተወካይ ሁሉንም የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ማስታወቂያዎች/ዘገባዎችን ወዲያውኑ ይ/ትመረምር እና ማረምያ እርምጃዎችና ውጤቶችን እነደኣግባቡ ይ(ት)ተገብራል/ለች።

b) የት/ቤት ኣስተዳዳሪዎች በማሸማቀቅ ኣድራጎት የተሳተፉ ተማሪዎች ወላጆች/ኣሳዳጊዎችን ወድያውኑ ያሳውቋቸዋል።

c) ምርመራው እንዳከተመ፣ የሰራተኛ ኣባሎች ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ቀጥሎ እንደሆነ ለመወሰን ከተጠቂ እና ከኣጥቂ ተማሪ ከሁለቱም ጋር ግላዊና ሚስጢራዊ ስብሰባዎች ያካሂዳሉ።

5. ለተጠቂ ተማሪ፣ ለኣጥቂ ተማሪ፣ እና ለዳር ቁሞ ተመልካቾች የሚቀርቡ የድጋፍ ኣገልግሎቶች

ኣንድ የማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ኣድራጎትን በማስመልከት ከሰራተኛ ኣባል ጋር ለመወያየት ኣንድ ተማሪ ምኞቱን ከገለፀ፣ የሰራተኛው ኣባል ተማሪውን ስራ ማዋል የማያስቸግር፣ ደህና/ኣስተማማኝ፣ ግላዊ፣ እና ከእድሜ-ጋር-ኣግባብ ባለው መንገድ ለመተግበር ጥረት ያደርጋል።

ስርኣቱ ለተማሪዎችና ለቤተሰቦች የሚጠቁ ተማሪዎች፣ የሚያጠቁ ተማሪዎች እና ዳር ቁሞ ተመልካች የሆኑ ተማሪዎች በት/ቤቶቹና በማህበረሰቦቹ በሁለቱ ውስጥ ሊያገኟቸው የሚችሉ ኣገልግሎቶች ዝርዝር በቅርብ እንደሚያገኟቸው ያደርጋሉ።

## D. ተፈላጊ ውጤት

ከማሽማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ነፃ የሆነ ትምህርታዊ አካባቢ ለመፍጠር ት/ቤቶች የመከላከያና የጣልቃገብነት ስልቶች፣ እንዲሁም ውጤቶችና ድጋፎች ያቀርባሉ።

## E. የትግባሬ ስልቶች

1. ይህን መመርያ ለመተግበር ደንቦች የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የሚያ(ምታ)ዳብር ሲሆን የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ ሰራተኛ በMCPS የዘገባና የምርመራ ሂደቶች እውቅና ያለው/ላት ስምና አድራሻ ለይቶ ያስታውቃል/ታስታውቃለች፤ የማሽማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት አድራጎቶች ማስታወቅ/ዘገባና ምርመራ ቅደም-ተከተሎች፤ ለተሸማቀቁ ተማሪዎች፣ ለአሸማቃቂ ተማሪዎች፣ እና ለዳር ቁሞ ተመልካች ተማሪዎች የሚቀርብ ድጋፍ፤ ውጤቶች ወይም ማረሚያ ትግባሬዎች፤ እና የነዚያ ሂደቶች/ቅደም-ተከተሎች ህትመትና ማስታወቅ ሂደት።

2. ይህን መመርያ ለመተግበር እና ማሽማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት በት/ቤቶች ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ለተማሪዎችና ለሰራተኞች ትምህርታዊና ሙያዊ እድገት ፕሮግራሞች ያዳብራል/ታዳብራለች።

3. በቦርድ-የፀደቁ መመርያዎችን በመደገፍ የዳበሩ ሁሉም ደንቦች እንዲያውቁት ለቦርዱ ይላካሉ።

## F. ግምገማ እና ዘገባ

ይህ ደንብ በቦርድ ድህረ እይታ ሂደት መመርያ መሰረት ይገመገማል።

**የተዛመደ ምንጭ፡-** *የሜሪላንድ ኣኖቴትድ ኮድ፣ የትምህርት ኣንቀፅ፣* §7-424.1

***የመመርያ ታሪክ፡-*** በውሳኔ ቁ. 132-10፣ ማርች 9፣ 2010 የፀደቀ ኣዲስ መመርያ፣ በውሳኔ ቁ. 489-16፣ ኖቨምበር 15፣ 2016 የተሻሻለ፣ ቴክኒካል መሻሻሎች በውሳኔ ቁ. 319-17፣ ጁን 26፣ 2017።